# የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ)
# UNITED ETHIOPIAN DEMOCRATIC FORCES (UEDF)

የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ) የዶክተር መኮንን ቢሻውን ከዚህ ዓለም በሞት መለየት የሰማው በከፍተኛ ሃዘን ነው።

ውድ አገራችን ኢትዮጵያ ካፈራቻቸው እውቅ ምኁራን አንዱ የሆኑት ዶ/ር መኮንን ቢሻው ከተማሪነት ዘመናቸው ጀምሮ እስከ ዕለተ-እረፍታቸው ድረስ ለወገናቸው የኢትዮጵያ ሕዝብ ሰብዓዊ መብትና ክብር መጠበቅ፥ ለዜጎች እኩልነትና ለሕግ የበላይነት መረጋገጥ፥ ለአገራቸው አንድነትና ለብሔራዊ ሉዓላዊነት መከበር ሳይታክቱ የታገሉ ኩሩና ጨዋ ዜጋ ነበሩ።

አረመኔውና አርቆ ማየት የተሳነው የአቶ መለስ ዜናዊ ጠባብ ቡድን ደርግን በተካ ማግሥት ፀረ-ሕዝብና ፀረ-ብሔራዊ ተቋማት እርምጃውን ሲያጧጡፍ የበሰለ እውቀትና የዳበረ ልምድ ያላቸውን አንቱ የተሰኙ አገር-ወዳድ ምኁራንን ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ድንቁርና በተሞላው ግፍ ሲያባርር ይኸ የጅል ዱላ ካረፈባቸው እውቅ ምኁራን መኻል ዶ/ር መኮንን አንዱ ነበሩ።

ዶ/ር መኮንን ቢሻው የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ጉባዔን (ኢሰመጉን) እና የመላ ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅትን በዋና ፀሐፊነት አገልግለዋል።

ዶ/ር መኮንን ለሁላችን ቤት የሆነችውን አገራችንንና በአምባ-ገነኖች አዙሪት ተጠምዶ ዝንታለም ፍዳውን የሚቆጥረውን ሕዝባችንን ለመልካም አስተዳደርና ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ባለቤትነት ለማብቃት የሚደረገውን የረጅም ጊዜ ትግል መልክ ለማስያዝ ታስቦ የተበተነውን የተቃዋሚ ጎራ አንድ ላይ በማምጣት የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረትን የመሠረተው በሐምሌ ወር ፲፱፻፺፰ ዓ/ም የተካሄደው የተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች አገር-አቀፍ ጉባዔ ላይ ድርጅታቸውን መኢአድን በመወከል ተገኝተው ከፍተኛ አስተዋጽዖ ያደረጉ የኅብረታችን መሥራች ነበሩ።

የሕግ-የበላይነት ለሰፈነባት፥ የዜጎች እኩልነት በውን ለሚከበሩባትና ሕዝቡ የሥልጣኑ ባለቤት ለሚሆንባት፥ አንድነቷ ለተጠበቀ ኢትዮጵያችን ዕድሜአቸውን ሙሉ ታግለው፥ የታገሉለት አገራዊና ሕዝባዊ ክቡር ዓላማ እውን መሆኑን በሕይዎት ዘመናቸው ሳያዩ፥ በወገን መኻልና በአገር ላይ ሳይሆን በእንግልትና በባዕድ አገር፥ በድሎት ሳይሆን በስቃይ፥ የተለዩንን አገር-ወዳድ ምኁር ኢትዮጵያውያን ሁሉ ስናስብ አገራችን ምን ያህል የወላድ መካን እንድትሆን እንደተፈረደባት ያረጋግጥልናል።

"ዞሮ ዞሮ ከቤት፥ ኖሮ ኖሮ ከመሬት" እንዲሉ ማንም ይሁን ማን ከሞት የሚቀር ባይኖርም እንደ ዶ/ር መኮንን ቢሻው የመሰሉ አገር-ወዳድ ምኁራን በአገራቸው ላይና በወገናቸው በኢትዮጵያ ሕዝብ መኻል ሆነው ያላቸውን በሳል እውቀትና የካበተ የረዥም ጊዜ ልምድ በሙሉ ነፃነትና ያለ ስጋት ለቀጣዩ ትውልድ እንዲያካፍሉ ሁኔታዎች አለመፍቀዳቸው በደሉ በግልና በተናጠል ሳይሆን በአገርና በሕዝብ ላይ መሆኑ አያጠራጥርም።

ኢዴኃኅ ለዶ/ር መኮንን ቢሻው ቤተሰቦች፥ ዘመድ አዝማድና ለትግል ጓደኞቻቸው ሁሉ ጥናቱን ይስጣችሁ እያለ ልባዊ የሐዘን ተካፋይነቱን ይገልጻል።

የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ)

የካቲት ፲፰ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ/ም


ዋና መሥሪያ ቤት (Main Office)
ፖ.ሣ.ቁ./P.O.Box 73246
Washington, D.C. 20056-3246,U.S.A
ስልክ/Tel.: 202-291-4217;
ፋክስ/Fax: 202-291-7645

ኢትዮጵያ (Ethiopia)
ፖ.ሣ.ቁ./P.O.Box
Addis Abeba,Ethiopia
ስልክ/(Tel.) 251_______
ፋክስ/Fax:2511________

አውሮጳ (Europe)
Jonathan Str. 82
2524 JJ The Hague,
Netherlands
Tel/Fax 31 70 394 6132